## ፓኖራማ ቁጥር 98

## የዝብት አድማስ

ጥቅምት 10 ቀን 2003 ዓም

# <u>ሎሌ በአፍላው የአህያ መኾገር ይከላል</u>

በኢትዮጵያ የተነሰራፋው የዘረኞች ሥርዓት አራማጅ ቡድን አለቃ ሰሞኑን የሥርዓቱ ታማኞች ይሆናሉ ላላቸው አዳዲስ አገልጋዮች ሹመት መስጠቱን ይፋ አድርጓል ፡፡ እነኝህ ገለሰቦችም ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀስፎ ለመግዛት በአዲስ መልክ ለተደራጀው ሥርዓት የወንጀል ተባባሪ ለመሆን ቃለ-ማሃላ መውስዳቸውን አረጋግጠዋል ፡፡ እነዚህ አዲስ ታማኝ አገልጋዮች የተሾሙት ፥ ገዲሞቹ የህወሃት/ ወያኔ አገልጋዮች እንደ አሮጌ ቁና ከተወረወሩ በኋላ ነበር ፡፡ ይህ በወያኔዎቹ ቲያትር አዳራሽ የተከናወነው የሰሞኑ ተውኔት፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሳያስደንቀው አልፏል ፡፡ አዲስ ድራማ ስለአላየ ነበር ያልተደነቀው ፡፡ይህ የራሱን ልጆች እንደ ድመት እየቀረጠፈ የሚበላ ሥርዓት ሂደት፥ ለአለፉት አርባ ዓመታት በሀገራችን የተለመደ የአምባገነኖች ሥልጣን መደላደለና መቆጣጠር ስልት በመሆኑ፥ የፖለቲካ ሀሁ የቆጠረ ዜጋ ሁሉ የሚገነዘበው ክስተት ነው ፡፡ ታዲያ ወያኔዎቹ ከደርግ ሥርዓት የወረሱትን “ እርስ በርስህ እየተበላላህና እየተጠፋፋህ በጥሎ ማለፍ ዘዴ የሥርዓቱን ዕድሜ እየቀጠልክ ግዛ ! ” የሚለው መርኅ ለሀገራችን ሕዝብ ዕንግዳ አይደለም ፡፡ የአምባገነነኖች ዓይነተኛ በጎርይና ተግባር ደግሞ የኸው ነው፡፡ ደርግም ይኸንን ሲያደረግ ቆይቶ ነው ፥ በመጨረሻ ወደማይቀረው ከርሰ-መቃብሩ የሄደው ፡፡በአምባገነኖች አገዛዝ ስር የሚያገለግሉ ሁሉ ፥ ታማኝነታቸው ያው ለኮለኮላቸው ሥርዓት በመሆኑ፥ዕድሜያቸው የሚወሰነው፥ታማኝነታቸውና አገልግሎታቸው እስከጠቀመ ድረስ ብቻ ነው ፡፡ ያምባገነን ሥርዓት ደግሞ ፥ ታማኝነታቸውን እያሳዩ የሚያገለግሉ ግለሰቦችን በገፍ ያገኛል ፡፡<u>ኅሌናውን፥ሰብዕናውንም ሆነ ጭንቅላቱን ለማስገዛት ፈቀደኛ የሆነ ሁሉ ፥የአፍላ ዘመኑ እስኪያልቅ ድርስ የአህያ መኾገር እስከ መክላት ድረስ ለአምባገነን ሥርዓት ያገለግላል ፡፡</u> “ ሎሌ በአፍላው የአህያ መኾገር ይከላል ” የሚባለውም እኮ ለዚሁ ነው !

የሰውን ልጅ፥ ከሌሎች ፍጥረቶች ሁሉ የተለየ ያደረገው ታላቁ መለያ ፥ ራሱ የአዕምሮውና የኅሊናው ተገኾርና ለነፃነቱም ቀናዒ መሆኑ ብቻ ነው ፡፡ ፈረስ ፥ በቅሎና፥ አህያ ጀርባቸውን ለኮረቻ ፥ጫንቃቸውን ለሸክም ፥ ወገባቸውን ለጭነት ፥ ደንደሳቸውንም ለቀንበር በማቅረብ ለጌቶቻቸው ሰጥ ለጥ ብለው የሚገዙት ፥ለሰው ልጅ ሁሉ የተሰጠው ኅሊና፥ አዕምሮና ነፃነት ስለአልታደለቸው ብቻ ነው ፡፡ ሰብዓዊ ፍጡር ፥ ለመኖር ብቻ ሲል የሚኖር ካልሆነ በቀር ፥ ነፃነቱን ማስገፈፍ ፥ አዕምሮውን ማስደፈር ፥ ጭንቅላቱን ማስገዛት አይኖርበትም ፡፡ ይህን ካደረገ ሰብዕናውን ለውጦ ወደ እንስሳ ደረጃ ዝቅ እንዳለ ሊያወቅው ይገባል ፡፡አንድ ሰው ጭንቅላቱን ለሌሎች ማስገዛት የጀመረ ዕለት ሰብዕና ኖሮት በህይወት ይኖራል ማለት አይቻልም ፡፡ ማንም ሳይገድለው ራሱን ራሱ አጥፍቶታልና !

የአምባገነን ሥርዓት ታማኝ በመሆን የሀገርና የሕዝብ ጥፋት አባሪ ተባባሪ ሆኖ መገኘት ፥በታሪክና በህግ የሚያስጠይቅ ከባድ ብሔራዊ ወንጀል ነው ፡፡ በታማኝ ተቃዋሚነትና በትግል ሽፋን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ከሆነው ከወያኔ ዘረኛ ሥርዓትጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋሪ መተባበር ከሕዝባዊ ፍርድ ነፃ ሊያደርግ አይችልም ፡፡ የወያኔ ጦር መሳሪያ ክምችት ፥ የሕዝብጨፍጫፊ ሠራዊት ጋጋታ፥ የስለላ መረብ መዘርጋት ፥ የባዕዳን ርዳታ መጉረፍ ፥ የጥቁር ፕሮፓጋንዳ ማደንቆር ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሞራልና ወኔ ሊሰብረው አይችልም ፡፡ የኢትዮጵያን ኅላዊ የመጠበቅ ዋስትናውም ሆነ መሠረቱ ደግሞ የሕዝቡ ወኔ

፥ ኩራትና ነፃነቱንም ላለማስደፈር የሚያሳየው አይበገሬነት ነው ። ይህንንም ለአለፉት አርባ ዓመታት በተፈራረቁት አምባገነን ሥርዓቶች ወቅት አስመስክሯል ።

**በየዓመቱ በሚመጣው የበልግ ወራት፥እባብ አሮጌ ቆዳውን እየሸለቀቀ እንደሚጥለው ሁሉ፥ ወያኔም እንደዚሁ፥ አግልግሎታቸውን የጨረሱ ተባበሪዎቹን እንደ አሮጌ ቆና አሽቀንጥሮ በመጣል በአዲስ አገልጋዮች እየተካ በሥልጣን የመቆየቱን ስልት ጎንጉኖ ጨርሷል ።የሰሞኑ ሹም-ሽር የዚህ መሰሪ ስልትና እኩይ ተግባር ውጤት ነው።** *ሂደቱም ዘዴውን እየቀያየረ ይቀጥላል ። በሕዝብ አመፅ እስከሚደመሰስ ድረስም የሕዝብ ተስፋና ምኞት እንዲደበዝዝ የጭቆና መሳሪያውን ያጠነክራል ። " የኋላ-ኋላ ወያኔን አያድርገኝ " ብሎ አድፍጦ የሚጠባበቀው ዕምቅ ሕዝባዊ ኃይል ነገ- ተነገ ወዲያ ምን እንደሚያደረግ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው የሚያውቀው ። ወያኔና ተባባሪዎቻቸው ግን ፥ ዛሬ ይህን አርቀው እንደማይመለከቱ ዐይነ- ኅሊናቸው ተሰውሮባቸዋል ። አርዕድ-አንቀጥቅጥ ለውጥ የሚመጣው ፥ መሳሪያ ባነገበ ቡድን ብቻ እንጅ፥ በሕዝባዊ አመፅ ሊመጣ አይችልም ብለው ደምድመዋል ። ወያኔዎቹ ፥ የየካቲት 1966ቱን ሕዝባዊ አመፅ ስለአላዩ ፥ ስለአልተካፈሉ ፥ በቦታውም ስለአልነበሩ ከዚህ ድምዳሜ ቢደርሱ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይገርመውም ። ምክንያቱም፥ " ኢትዮጵያ ከአንድ መቶ ዓመት ወዲህ የተፈጠረች ሀገር ነች " ያሉ ባዕድ- መሰል ዜጎች በመሆናቸው፥ ስለ ሀገሪቱ የቅርብም ሆነ የሩቅ ታሪክ ደንታ ስለሌላቸው ነው።*

*የወያኔ መሪዎች፥ የተሻሩትም ሆኑ ፥ አሁንም ሥልጣኑን ይዘው የቀጠሉት ሁሉ አንድ የሚስማሙበት መሠረታዊ ጉዳይ አላቸው። ይኸውም ወያኔ የመሠረተው ሥርዓት በምንም ዓይነት ሁኔታ እንዲለወጥ አይሹም። በይዘትም ይሁን በቅርፅ እንዲለወጥ አይፈልጉም።ይህን ማሰብ ማለት ለእነርሱ የትግራይን የበላይነት መሸርሸር ማለት ነው። ለነርሱ፥ ይህ የሥርዓት ለውጥ የሚታሰብም፥ የሚሆንም፥ የሚደረግም አይሆንም። ለዚህ ሦስት ዐበይት ምክንያቶች አሏቸው። እነርሱም ፦*

1. *የሥርዓት ለውጥ ከመጣ፥ በተለያዩ ከባድ ብሔራዊ ወንጀሎች እንጠየቅአለን ብለው ይፈራሉ ። ሀገር ከማስገንጠል ጀምሮ ፥ የዘር ማጥፋትን አካትቶ ፥ ብሔራዊ ሀብት መዝረፍን አጠቃልሎ ባሎት ወንጀሎች በሙሉ መጠየቃችን አይቀርም ብለው ይፈራሉ ። በወንጀል ተጠያቂ እንዳይሆኑ፥ አስተማማኝ ዋስትናው ፥ ሥርዓታቸውን አጠንክረው በሥልጣን መቆየት ነው ብሎው ያምናሉ። የትግራይን የበላይነት አስፍኖ መቀጠል ለህይወታችን ማረጋገጫ ነው ብለው ራሳቸውን ይደልላሉ ። በመሆኑም ሥርዓቱ ሳይናጋ መቆየት እንዳለበት ማንም ሳይመክረቸው ፥ እነርሱ እራሳቸው ያውቁታል።*

2. *ወያኔና ተባባሪዎቻቸው ለአለፉት* 19 *ዓመታት የሀገሪቱን ብሂራዊ ሀብት በሙሉ ዘርፈዋል ። ልኩና መጠኑ የማይታወቅ የሀገር ሀብት ወደ ወጭ አሸሽተዋል ። ይህ የተዘረፈ ሀብት ጉዳይ እንደ እግር እሳት ያነገበግባቸዋል ። ይህን ሀብት ማጣት አይፈልጉም ። " ማን የዘረፈውን ማን የወስደዋል " የሚል ትዕቢት ተጠናውቷቸዋል። በመሠረቱ ያ የዘረፉት ሀብት የኢትዮጵያ ብሂራዊ ሀብት መሆኑን ማሰብ ቀርቶ መስማት እንኳን አይፈልጉም ። ሥርዓታችን ከተለወጠ ከጎንደር ፥ ከወሎና አፋር ግዛቶች የወሰድነው መሬት ወደ ቦታው ይመለሳል ብለውም ያምናሉ።*

3. *እኛ በሰራነው ሥራ " በሕዝባችን ( በትጋራይ) ላይ የበቀል ርምጃ ይወስድበታል " የሚል መጠየቂያ በመፈለግ ሥርዓታችንን አጠንክረን መቀጠል አለብን ብለው ያምናሉ ። ይህ መሳሰፈራሪያ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ ያስተባብርልናል ከሚል ቅዠት ውስጥ ጥሏቸዋል ። ይኸንን አስመልክቶ ፥ አንድ ያልተገነዘቡት ነገር ቢኖር፥ በወያኔ ወንጀል ምክንያት የትግራይና ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ በምን ምክንያት በክፉ ዓይን የማይታያይ መሆኑን ነው ። በታሪኩና ባጎሉ ፥ ለፍትሕ-ርትዕ ለዳኝነትና*

በመልካም ሁኔታ አብሮ መኖርን ያነገበ ሕዝብ፥ አምባገነኖች ባመጡት ጥፋት ዕርስ በዕርሱ እንደማይጋጭ አኩሪ ታሪኩ ይመሰክረለታል። ይህማ ባይሆን ኖሮ በወያኔ የዘር ካርድ ፖለቲካ የሀገሪቱ ሁኔታ ሌላ ቅርፅ ይኖረው ነበር።

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች፥ ወያኔዎቹ የዘረጉት ዘረኛ ሥርዓት እንዲለወጥ አይፈልጉም ። መለስ ከሥልጣን ያገለላቸው የወያኔ ባለሥልጣኖች ከሹመታቸው ወረዱ አልወረዱ፥ መስፍን፥ በመኮንን፥ አባዱላ በአብደላ፥ ስብሀት ነጋ በጣሰው ቢረጋ፥ ወዘተ ቢለወወጡ ፥ ቢከረባበቱ ፥ አሁን ባለው የሀገሪቱ የፖለቲካ መልክዐ- ምድር ጭራሽ የሚያመጠው ሁነኛ አንደምታ አይኖርም። ወያኔም፥ በፖለቲካ፥ በኢኮኖሚ፥ በማኅበራዊ ኑሮ የሚያሻሽለው ነገር ያመጣ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም ። ይህን የሚጠብቁ ካሉ፥ የተሰፋ ዳቦ ለመግመጥ የሚያቋምጡ ብቻ ናቸው ። የሀገሪቱም የውስጥና የውጭ ፖሊሲ የምዕራባውያንን ጥቅምና ብዝበዛ እስከጠበቀ ድረስ እንዳሁኑ እንዳለ ይቀጥላል ። የሥርዓት ለውጥ እስከሌለ ድረስም፥ የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች መወገድ ቀርቶ፥ ሊቀረፈቱ እንኳ አይችሉም ። የኽንንም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም ሳያወቀው ራሱ በሚገባ ያውቀዋል ። ለዚህም እኮ ነው ዛሬ ፦

“ እናንተ እንዴት ናችሁ እኔ እንዳለሁ አለሁ ፥
ችግር ተሸካሚ ካሚዮን ሆኛለሁ ! ”

እያለ የመካራ ጩኸቱን የሚያስተላልፈው ። በኢትዮጵያ ሀገራችን ስር- ነቀል ለውጥ እስካልመጣ ድረስ፥ የሀገራችን ሕዝብ መከራ እንደሚቀጥል ታውቆ፥ ወያኔን ማስወገድ፥ ምን ጊዜም ቢሆን ከኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል አጀንዳ ግንባር- ቀደሙን ቦታ እንዲይዝ መደረግ አለበት ። ሌላው ሁሉ ዝባ-ዝንኪ ነው ። የሥርዓት ለውጥ መምጣት ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችንን፥ ከአዜው ኋላ ቀር አገዛዝና ከደርግ ፋሽስታዊ ጭቆና ነፃ እንዳወጣት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም ሊነግረው አይችልም ። የወያኔም ዘረኛ ሥርዓት የሚጠብቀው ዕድል ይህንኑ ነው ።ሥርዓቱን ለማቆየት አፍለኛ ሎሌዎቹን መኮልኮል፥የአህያ መኽግር ከመክላት የበለጠ ተግባር አይከናወንም ። የሚበሰብስን ሥርዓት ደግሞ ምንም ዓይነት ቀድዶ-ጥገና አያድነውም ። በሕዝባዊ አመፅ ግን ይደመሰሳል ።